★ዴሞክራሲያ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞ ቅጽ 44 ቁ. 5 ሰኔ/ሐምሌ 2011 ዓ.ም

# የምርጫ ቧልት አባዜ

ለግማሽ ምዕተ ዓመት ያህል ሕዝብ የሥልጣን ምንጭ የሚሆንበትን ሥርዓት እውን እንዲሆን ሲካሄድ የነበረውና ኢትዮጵያውያን እስከዳር የተሳፉበት ሕዝባዊ ትግል ላለፉት እነዚህ ዓመታት የእልህ አስጨራሽ ጉዞ ያለማቋረጥ ቢያደርግም እስካሁን በድል ሊጠናቀቅ አለመቻሉ ግልጽ ነው። ኢሕአፓ ልሳኑ በሆነው ዴሞክራሲያ፣ በተለያዩ የዘወትር መጣጥፎቹና በሌሎችም የመገናኛ ዘዴዎቹ፣ የሕዝባዊ ትግል ግብ የሆነው የሥርዓት ለውጥ እውን ያልሆነባቸውን ምክንያቶች በየምዕራፉ ሲዘረዝር፣ ሲተነትንና ሲጠቁም፣ አደጋዎችን ሲያስገነዝብና አቅጣጫንም ሲያመላክት መቆየቱም ይታወቃል። ቀደም ብሎ በተሰራጩት የዴሞክራሲያዊ እትሞች የተስተናገዱት ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆነው በአሁኑ ወቅት አገራችን ያለችበትን ሁኔታ ድርጅታችን ኢሕአፓ እንዴት ያየዋል? ዋና ዋና ችግሮቹስ ምንድናቸው? ችግሮቹንስ ለማስወገድ የሚረዱ እርምጃዎችስ ምን ሊሆኑ ይገባል? የሚሉትንና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን በዚህ የዴሞክራሲያ እትም እናነሳለን፡፡

እነሆ የአስራ ሰባት አመታት ፋሽስታዊ ወታደራዊ አገዛዝ፣ እጅጉን ያስመረረው የኢትዮጵያ ሕዝብ የባሰ አይመጣም በሚል እሳቤ ተዘናግቶም ሆነ ግራ ተጋብቶ፣ የነበረበት ወቅት ላይ፣ ወያኔ ይህን አጋጣሚና ሙሉ የባእድ ኃይላትን፣ እንደ አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ሱዳን፣ ስዊዲን፣ ኖርዌይ፣ ...ወዘተ ድጋፍን በመጠቀም፣ ሥልጣን ለመቆጣጠር ቻለ። በባዕድ ኃይሎች ድጋፍና ትብብር ወያኔ በጠመንጃ ኃይል ሥልጣን ከተቆጣጠረ በኋላ ዛሬ ኢትዮጵያ ለገባችበት ቀውስ ዋናና አብይ ምክንያት የሆነውን የከፍፍል ሥርዓትም ለመዘርጋት በቃ። ባለፉት ሃያ ስምንት ዓመታት አገራችን የዘረኝነትና የከፋፋይነት አባዜ ተጭኖባት፣ በረዥም ጊዜ ታሪኳ ውስጥ አንዳችም ጊዜ ገጥሟት በማያውቅ አስከፊና አደገኛ ሁኔታ ውስጥ እንድትገባ ተገደደች። ውስብስብ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበረሰባዊ ችግሮቿ ብቻ ሳይሆኑ፣ እንደ ሃገር እንዳትቀይ ህልውናዋን አጥብቀው የሚፈታተኑም እንቅፋቶች በየአቅጣጫው እያተራመሷት ይገኛል። ዘርንና ቋንቋን መሠረት ያደረገው የወያኔ/ኢሕአዴግ አገዛዝ ፀረ ሕዝብ፣ ፀረ ኢትዮጵያ፣ ፀረ ዴሞክራሲ በመሆኑ፣ ፖሊሲዎቹም ሆኑ ሁሉ እቅዶቹ የቡድኑን መሠረታዊ እምነት ተግባራዊ ማድረግ ላይ ያጠነጠኑ ነበር። የወያኔው ቡድን ገና ሥልጣን ሲይዝ የተቃወሙትንና የታገሉትን ሁሉ የአፈና፣ የግድያ፣ የሽብር፣ የእስራት፣ ...ወዘተ ወንጀሎች ሲያካሂድባቸው መቆየቱ የሚታወቅ ሲሆን ዛሬም ቢሆን ቡድኑ ከዚህ አረመኔያዊና እኩይ ተግባሩ ሳይቆጠብ በወንጀሉ የቀጠለ መሆኑ ግልጽ ነው። ከኢትዮጵያ የተገነጠለች የትግራይ ሪፐብሊክ ለመመስረት አንደ ዋና ዓላማው አድርጎ እንቅስቃሴ የጀመረው ወያኔ፣ ባለፉት 28 ዓመታት በጠመንጃ ኃይል የተቀረውንም የኢትዮጵያ ግዛት መቆጣጠር ቢችልም ይህንኑ የመገንጠል አጀንዳውን ካርድ ለመሳብ እንዲረዳው የሚያስችለውን አንቀፅ በሕገ መንግሥቱ ውስጥ እንዲካተት ማድረጉ አይዘነጋም። ዛሬ ላይ ከወያኔ መንደር ይህን አስመልክቶ እየተደለቀ ያለውን ማስተዋሉ ተገቢ ይመስለናል።

ዘመናትን ተሻግሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ የአንድነት መስተጋብር የሰረፀው፥ ሕዝቡ በዘመን ሂደት ውስጥ እንደሌሎች የዓለም ሀገራት ሁሉ አገርን ለመመስረት የሚጠይቀውን ከፉም ሆነ በጎ ሁኔታን አብሮ መካፈሉ፥ መደጋገፉ፥ መነሳቱና መውደቁ፥ ብሎም የውስጥም ሆነ የውጭን ጠላት በጅግንነት መከቶ፥ ነፃና የራስ የሆነች አገር እንድትኖር ባደረገው ከፍተኛ ተጋድሎ ውስጥ እንደሆነ ታሪክ የመዘገበው ነው። እናም ይህችን አጥንቱን ከስክሶ ደሙን አፍስሶ ያቆያትን ታላቅ ሃገር፥ ከትውልድ ትውልድ እያሻገረ በነፃነት ታፍራና ተከብራ እንድትቆይ አድርጓል። ኢትዮጵያ በርካታ ባህሎች የሚስተናገዱባት፥ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች የሚነገሩባት፥ ትላልቅ ሃይማኖቶች የሚመለኩባት ብቻ ሳትሆን፥ ለዘመናት በሌሎች የዓለም ሃገራት ሃይማኖትን ተንተርሶ የሚፈጠር ችግር አንፃራዊም ቢሆን ከቶ ያልደረሰባት አገር ሆና እስካሁን ዘልቃለች። አንዲት ጥቁር አገር የነጭ ዘር የሆነውን ጣሊያንን በአድዋው ጦርነት ድባቅ መታ የነጭን ዘር አዋረደች ከሚል እና ኢትዮጵያ ያለችበት ጂኦግራፊያዊ ክልል ያለውን ስትራተጂክ እንደምታ ከግምት ውስጥ በማስገባት፥ የባዕድ ኃይሎች ጥንትም ሆነ ዛሬ ጥቅማቸውን ጥያቄ ውስጥ ሊጥል የሚችል፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይሁንታ ያገኘና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅምና ለኢትዮጵያ ህልውና አበክሮ በፅናት የሚቆም ኢትዮጵያዊ የመንግሥት ኃይል፥ በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ እውን እንዳይሆን አበክረው ሠርተዋል። ዛሬም እየሠሩ ይገኛሉ። በታሪካችን ዛሬ እስከደረስንበት ታሪካዊ ወቅት ድረስ፥ የባዕድ ኃይላት በማን አለብኝነት በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እየገቡ ዜጎቿን እርስ በርስ የማጋጨት፥ የማናቆር፥ ሰላም የሚነሳና የሚያምስ ድርጊት ሳያሰልሱ ፈፅመዋል። አሁን በምንገኝበት ወቅት ላይም ቢሆን ከዚህ እኩይ ተግባራቸው ከቶ ሊታቀቡ አልቻሉም።

አገራችን ኢትዮጵያ እጅግ አኩሪ ታሪክ ፥ ከመቶ ሚሊዮን በላይ የሚቆጠር የሕዝብ ካፒታል ፥ ተዝቆ የማያልቅ የተፈጥሮ ሃብት የተለገሰች ውብ አገር ለመሆኗ የሚያከራክር አይደለም። ይህ ገፅታዋ እንደተጠበቀ ሆኖ፥ በሌላ በኩል ግን በታሪክ ሂደት ውስጥ ከመልካም አስተዳደር እጦት የተነሳ፥ በህዝብ ላይ የደረሱ ልዩ ልዩ በደሎች እንደነበሩ ከግልጽም ግልጽ ነው። በባህላቸው፥ በሃይማኖታቸው የተነሳ የሚበደሉ፥ ለብዝበዛ የተጋለጡ፥ ጥረው ለፍተውም በድህነት አረንቋ እንዲማቅቁ የሆኑባት አገርም ነበረች። ዛሬም በምድር ላይ ያለው ሁኔታ ከዚህ የተለየ እንዳልሆነ ለሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተደበቀ አይደለም። እነዚህን አስከፊ ገፅታዎች ለመለወጥ ነበር በ1966 ዓም በየካቲት ወር ላይ ለዘመናት ውስጥ ውስጡን ተዳፍኖ ሲንቦለበል የቆየው የሕዝብ ብሶት ድንገት ገንፍሎ ሳይታሰብ ከዳር እስከዳር በተካሄደ ሕዝባዊ አመጽ የአፄውን የጉልተኛ ሥርዓት ሊገረሰስ የቻለው። ታዲያ የፊዳሉ ሥርዓት ሲገረሰስ ወደ ሕዝባዊ ሥርዓት አሸጋጋሪ የነበረው የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ጥያቄ እስካሁን እውን ሳይሆን ቀርቷል። ለዚህ ዋናው ተጠያቂ ፋሽስታዊው ወታደራዊ አገዛዝና በወቅቱ ተባባሪው የነበሩት ልዩ ልዩ ፀረ ሕዝብ ኃይላት እንደነበሩ ቀደም ብሎ በሰፊው የተባለበት በመሆኑ፥ እዚህ ላይ ላለመድገም መርጠናል። ፋሽስታዊውን ወታደራዊ አገዛዝ የተካው የወያኔ/ኢሕዴግ አገዛዝ አትዮጵያን በታሪኳ ካጋጠሟት አገዛዞች ሁሉ ከፉኛ ያጠቃትና ያሽመደመዳት አገዛዝ ነው። ህልቆ መሳፍርት በደል አድርሶባታል። ሥልጣን የተቆናጠጠው የወያኔ ቡድን የሀገሪቱን አንጡራ ሃብት የውጭ አገር ባለ ሃብቶች እንዳሻቸው እንዲበዘብዙ እድሉን አመቻችቶ የጥቅሙም ተካፋይ በመሆን ሀብት አካብቷል። ከላይ እስከታች በሙስና ተጨማልቆ ጥቂቶች ከመጠን በላይ የተንደላቀቁባት፥ ከ99% በላይ የሆነው ህዝብ በድህነት በእርዛትና በበሽታ የተንሳቆለባት አገር ከመሆኗም ባሻገር፥ ፀረ ዴሞክራሲ የሆነው አገዛዝ የሚያስከትላቸው፥ የሥርዓት-አልበኝነት ባህሪያት - ዝርፊያ፥ የስነምግባር ዝቅጠት፥ ...ወዘተ - በመላ አገሪቱ መረን በለቀቀ ሁኔታ ተናኝተዋል። በመሆኑም የአገሪቱ ዜጎች በሰላም ከቤታቸው ወጥተው በደህና የሚመለሱባት ሁኔታ ባለመኖሩ ሕዝብ ሁሌም በስጋት እንዲኖር አስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ ገብቷል። ቡና ፈልቶ ፈልቶ መስከኑ አይቀርም ከሚሉን ለሕዝብ ንቀት ካላቸው ሹሞች በስተቀር ለሌሎቻችን ግን፥ ይህ ክስተት አሳሳቢና ትኩረትን የሚሻ አገራዊ ዋና ጉዳይ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም። የሚያውቀውን፥ የኖረበትንና እየኖረበት ያለውን፥ እንደመድገም አይቆጠርብንና የኢትዮጵያ ሕዝብ በወያኔ

ዘረኛና አምባገነን አገዛዝ ሥር፥ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቱ ሙሉ በሙሉ ተረግጦ፥ በነፃ የመደራጀት፥ የመፃፍ፥ የመሰብሰብና የመናገር፥ በእውቀቱና በችሎታው መጠን ሥራ ሠርቶ ራሱን ጠቅሞ በአገሪቱ የኢኮኖሚ ተሳትፎ ውስጥ ሊኖረው የሚገባውን የዜግነት ሚና ለመጫወት ያልቻለበት ሁኗል።

ከ2010 ዓም በፊት ባሉት ሦስት ዓመታት ውስጥ የወያኔ/ኢሕአዴግን አገዛዝ ለማስወገድ በርካታ መስዕዋትነትን የጠየቀ ትግል ተካሂዷል። በሙስና የላሸቀው የወያኔ/ኢሕአዴግ  አገዛዝ ከሻቢያ ጋር ባደረገው ጦርነትና በኋላም የመለስ ህልፈት ታክሎበት፥ የክፍፍልና አለመግባባት ሰለባ ለመሆን በመብቃቱ ተዳክሞ ስለነበር እንደቀድሞው የሚደርስበትን ተቃውሞና ትግል ለመቋቋም የሚችልበት አቅሙ እጅጉን እንዲሳሳ ሆነ። የሕዝቡ ትግልም የወያኔውን አገዛዝ አስወግዶ የሥርዓት ለውጥን ለማምጣት የሰነቀና ጠንካራ በመሆኑ የአገዛዙን በሥልጣን ላይ መቆየት በጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ሁኔታ ውስጥ ከቶት እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው።  ሙሉ በሙሉ ባይሆንም ትግሉን ያቀዘቅዙልኝ ይሆናል በሚል እሳቤ፥ የተወሰኑ የህሊና እስረኞችን፥ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅን፥ የሽብርተኛነት ሕግ አዋጅን፥ …ወዘተ ሰርዣለሁ እስከማለት ቢደርስም (ለነገሩ አዋጆቹን አልሰረዘም እስካሁን)፥ ትግሉ ጋብ ሊል አልቻለም፡፡  ተጠናክሮ የቀጠለው ትግል አገዛዙን ለማስወገድ ጠርዝ ላይ ደርሶ የነበረ ቢሆንም፤  ታማኝ አገልጋይ ሎሌያቸውን ፈጥኖ ለማዳን አሜሪካና ሳውዲ በቂ ዝግጅት የጠየቀ እቅድ በመንደፍ ሥራ ላይ በማዋል ትግሉን ማቀዝቀዝ ችለዋል።

እነሆ የዓመት ተኩል ዕድሜውን እየዘለቀ ያለው ያለንበት የአገሪቱ ሁኔታ፤ የማማለል ችሎታና ሁሉን አውቃለሁ በሚል፥ የሃገርንና የፖለቲካን ጉዳይ እጅግ አቅሎ በሚወስድ፥ ለመሠረታዊ ጥቅም የሚደረግን ግብግብ በፍቅርና በመደመር አባዜ መለወጥ ይቻላል የሚል ቲያትር እያየን ነው። ይህም አሜሪካኖች ሲያዘጋጁት የቆየን ኮረኔል በጠቅላይ ሚኒስተርነት ማዕረግ ከሾሙት ወዲህ፥ ወያኔ/ኢሕአዴግ የህዝቡን የሥርዓት ለውጥ ፍለጋ ትግል በቃላት ጋጋታ ለማድበስበስ ሆን ብሎ የተደረገ እንቅስቃሴ የተገኘ እንደሆነ ግልጽ ሁኗል። በጣም አስገራሚና ንቀት በተሞላበት መንገድ፥ በሙስና ተጨማልቂያለሁ፥ ሕዝብን ወደ ትግል እንዲገባ ያበቁትን ግፎችና በደሎች ሁሉ በተደጋጋሚ ገምግሜ እርምት ለማድረግ ተዘጋጅቻለሁ፥ ይቅርታም እጠይቃለሁ ያለው አገዛዝ ፥ የመፍትሄውን ፍለጋና መሪነት ለኔው ተዉት ብሎ ተፈጥሞብንም ይገኛል።

የለውጥ ኃይል ነኝ እያለ ከመቀላመዱም በላይ፥ ወደ ዴሞክራሲ ልትሸጋገሩ የምትችሉት በእኔ መሪነት እንጂ ነው እያለ በሕዝብ ላይ ተሳለቀ። ሹሙ ኮሎኔል ሳይፈራና ሳያፍር፥ ባለፉት ዓመታት የወያኔ አገዛዝ ውስጥ በደልና ግፍ የፈጸሙትን አስወግዶ የወያኔ/ኢሕአዴግን አገዛዝ ለማስቀጠል እንደሚሠራና ሕገ መንግሥት ተብየውም እንዲሁ ቀጣይነት የሚኖረው መሆኑን መግለፁ የሚዘነጋ አይደለም።  አንድ ዓመት ከግማሽ እድሜ እየተጠጋ ያለው በሹሙ እየተመራ ያለው እንቅስቃሴ አፉ ቅቤ ልቡ ጩቤ እንዲሉ ዓይነት ሆኖ እነሆ ቀድሞም ከሕዝብ ያልደበቀውን ጉዳይ አንድ በአንድ ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል።  መፍትኄ የተባሉትም በቅድሚያ የሹሙን ቡራኬ እንዲያገኙ ሆነው፥ ለሥርዓቱ ቀጣይነት የሚበጁት ሁሉ  በሥራ ላይ እንዲውሉ እየተደረገ ነው። እቅዱም ያለውን ሥርዓት ቀባብቶ ለማስጓዝ በሚያስችል ታሳቢነት የተቃኘ በመሆኑ እዛው ፈላ እዛው ሞላ ከመሆን የተለየ አልሆነም። ይህም ከላይ ልንጠቅሰው እንደሞከርነው የመከራችንን ቀጣይነት የሚያውጅ እንጂ ተስፋችንን የሚያለመልም ብሥራት እንዳልሆነ የምንስተው አይሆንም።

ዛሬ ላይ ሕግና ሥርዓት የማስከበር ሃላፊነት የጎደለበት፤ ብሔረተኝነት፥ ዘረኝነትና ጎጠኝነት እንደልባቸው የሚፈነጩበት፤ ለም ስፍራ ተመቻችቶላቸው፥ የሀገሪቱን ህልውና እየተፈታተኑ ያሉ ከመሆናቸው ባሻገር፥ እንደ ተጨማሪ ሁለተኛ መንግሥት ራሳቸውን በትጥቅ ሳይቀር አደራጅተው፥ የፈለጉትን ሁሉ በማድረግ ፥ በሕዝብና በአገር ላይ ልዩ ልዩ ወንጀሎችን ተው የሚላቸው በጠፋበት ሁኔታ እየፈፀሙ እንዳሉ የአደባባይ ምስጢር ከሆነ ሰንብቷል። መንግሥት ነኝ ባዩም በለውጥ ሂደት ውስጥ ባለች አገር፥ እንዲህ እንዲህ ያሉ ሁኔታዎች መከሰታቸው አይቀሬ ነው በሚል ስሌት ግዴላችሁም በሂደት ይከስማሉ ብሎ ይሳለቅብናል። በመሬት ላይ ያለው ሐቅ ግን ላለፉት ሀያ ስምንት አመታት በወያኔ/ኢሕአዴግ በመላ ሀገሪቱ ተተክሎ የቆየው የዘረኝነትና የክፍፍል መሰሪ ፖሊሲ ሲሆን ፥ ለዘመናት አብሮ የኖረውን ሕዝብ እኛና እናንተ በሚል ዘይቤ ከፋፍሎ እርስ በርሱ በክፉ እንዲተያይ፤ የጥላቻ ስሜት እንዲተከል ተጽእኖ ሲያደርግ መቆየቱንም አብሮ ልብ ይሏል፡፡ ከዚህ ፖሊሲ ተጠቃሚዎቹ የአገዛዙ ሹሞችና የለውጡ ደጋፊዎች ነን የሚሉ ልዩ ልዩ ቀለሞች ያነገቡ ክፍሎች እንዲሁም የተወሰኑ የመገናኛ ብዙሃን ተቋሞች ናቸው። የኑሮ ውድነቱ፥ መፈናቀሉ፥ ሥራ አጥነቱ ሕዝብን ያስመረረ ከመሆኑም በላይ ያለ ስጋት እንደ ልብ ወጥቶ መግባቱ፥ ከቦታ ቦታ እንዳሻ መንቀሳቀሱ የሚናፈቅበት ጊዜ ላይ ተደርሷል። ይህ ለማንም ጤነኛ ዜጋ ቅስም የሚሰብር ድባብ ነው። ዛሬ ላይ ያለችው ኢትዮጵያ ከአምባገነን አገዛዞች ራሷን ነፃ ለማውጣት ያደረገችው ትግል በመስቀለኛ ጎዳና ላይ ያለ ብቻ ሳይሆን ህልውናዋንም ጭምር ስጋት ላይ የሚጥል ሆኖ ይገኛል። ከዚህ ድባብ ለመውጣትና አትዮጵያንም ለመታደግ ምን ማድርግ ይበጅ ይሆን የሚለውን ጥያቄ በሰከነና ኃላፊነት በተሞላው መንገድ ለመመለስና ጉዳዩ የኔም ነው የሚል አትዮጵያዊ ሁሉ አርቆ አስታዋይነትን በተላበሰ መንፈስ እንዲያጤነው ጊዜው የግድ ይላል።

ኢትዮጵያ የሁላችንም የጋራ አገር ናት። ለገሚሱ እናት፥ ለቀረው የእንጀራ እናት እንድትሆንም አይጠበቅም። ይህ ሲባል ግን በየጊዜው እኔ አውቅልሃለሁ የሚሉ ኃይላት፥ የሥልጣን እርካቡን እየተቆጣጠሩ በሕዝብ ላይ በሚያደርሱት ግፍና በደል ፍዳቸውን የሚያዩ የህብረተ ሰብ ክፍሎች አልነበሩም ማለት እንዳልሆነ ግልፅ ነው። ዛሬም የሉም ማለት እንዳልሆነም ሁሉም ይገነዘባል ብለን እናስባለን። ይሁንና ይህን ሐቅ የማይቀበሉ መኖራቸውን ሳንዘነጋ! እኒህ በሕዝብ ላይ ግፍና በደል አድራሾች ግን ከጠቅላላው ሕዝባችን ቁጥር በልጠው የተገኙበት፥ በታሪካችን አንዳችም ጊዜ አልነበረም። ዛሬም ቢሆን ቁጥራቸው እዚህ ግባ የሚሉት አይደለም። እኒህ ክፍሎች ሁልጊዜም ከሕዝብ ጥቅምና ፍላጎት፥ ከሃገር ህልውናና ደህንነት ጋርም ተፃረው የቆሙ ናቸው። እስከ አሁን በተጓዝንበት የታሪክ ሂደት፥ ሕዝብ እነዚህ ኃይላት ሲያደርሱበት የነበሩትን ግፍና በደሎች ለማስቆም በዛም አነሰ ሳይታገላቸው የቦዘነበት ወቅት የለም። ዛሬም ይህንኑ ከማድረግ እንዳልተቆጠበ የምንመለከተው ነው።

ኢሕአፓ አንዱ የዚህ የሕዝብ ትግል አካል ሆኖ እየታገለ እዚህ ደርሷል። በዋናነት የታገለውም በዚህች የጋራ አገር በሆነችው ምድር ላይ ሕዝብ የማናቸውም ጉዳዮች የበላይ ወሳኝ መሆኑ በተግባር እንዲረጋገጥ ነው። አለመታደል ሆኖ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን የማይገረሰስ መብቱን በታሪኩ አንዳችም ጊዜ በሥራ ላይ ሊያውል የቻለበት ወቅት ገና አላጋጠመውም።

የመከራ ዘመኑ አላጥር ብሎ ዛሬም ድረስ ሕዝብ ይህን የማድረግ አቅሙን የተገነዘቡ አምባገነኖች፥ አድር ባይ ምሁራን ነን ባዮች፥ የሥልጣን ጥመኞችና ወንበር ናፋቂዎች፥ ጎጠኞችና ፅንፈኛ ብሔረተኞች፥ በየዘርፉ እየታገሉት ይገኛሉ። የሕዝብ የበላይነትና ወሳኝነት በአገሪቱ ተረጋገጠ ማለት የእነዚህ ሁሉ ፀረ-ህዝብ ኃይላት ህልውና ከሰመ ማለት ስለሚሆን፥ እነሆ ዛሬ በእነዚህ ኃይላትና በሕዝብ መካከል ከፍተኛ ትግል እየተካሄደ ይገኛል።

እንደሚታወቀው የሕዝብ የሥርዓት ለውጥ ፍለጋ ትግል በተቀነባበረ ስልት እንዲቀዘቅዝ፣ ብሎም እንዲቆም ከሆነ ወዲህ፣ እንደ እባብ አሮጌ ቆዳውን ሽልቅቆ ብቅ ያለው አገዛዝ አልሸሹም ዞር አሉ ከመሆን የዘለቀ አለመሆኑን ብዙም ሳይርቅ እያከታተለ የወሰዳቸው እርምጃዎች በግልፅ አረጋግጠውልናል። እርምጃዎቹ ወትሮም የሥርዓቱን ነፍስ ዘርቶ ማስቀጠል ነበርና ይህንኑ ሕጋዊነት እንዲላበስ በሚል እሳቤ ፈጥኖ ምርጫ የሚሉት ቧልት እንዲደረግ ውሳኔ ላይ ተደርሶ፣ ኅጠኛውም፣ ወያኔ/ኢሕአዴጉም፣ አድር ባዩም፣ ...ወዘተ የሕዝብን ተሳትፎና ፍላጎት ወደ ጎን በመተው፣ ይህንኑ ቧልት ለማሳካት በሚል እየተራኮቱ ይገኛሉ። የዚህ ትርምስ ዋና አላማው ለኢትዮጵያ ስርየትን ለማምጣት ሳይሆን ከፉውን የገለማውን አገዛዝ ጠጋግኖ ለማቆየትና ለማስቀጠል ብቻ ነው። በዚህ የምርጫ ቧልት ውስጥ ተሳታፊዎች ለመሆን እየተዘጋጁ ባሉ ኃይላት መካከል ምርጫው እንዲደረግ በተያዘው የጊዜ ገደብ መደረግ አለመደረግ አንስቶ በሌሎችም ጉዳዮች ላይ እየተጣረዙ ያሉ በመሆናቸው፣ ሂደቱ የንትርክ ሰለባ የመሆን እድሉ ሰፊ ነው ቢባል ስህተት አይሆንም። ምርጫ ተብየው ሂደቱና የሂደቱ ውጤት ፀረ-ዴሞክራሲ በመሆኑ ኢሕአፓ በፅኑ ይቃወመዋል። ለምን ቢባል፣ ሕዝብ እራሱ ፈቅዶ በመሰረተው ሕገ-መንግሥት አማካኝነት የመረጣቸውን መሪዎች መቆጣጠር የማያስችለው በመሆኑ፣ በመራጩ ሕዝብና በመረጠው ኃይል መካከል መተማመንን የሚነፍግ በመሆኑ፣ በምርጫዬ የሰጠሁህን ሥልጣን ተአማኒነትና ሃላፊነት በጎደለው ድርጊት የተነሳ፣ የሀገርንና የህዝብን ጥቅም በሚጎዱ ተግባራት ላይ በተከታታይ በመሰማራትህ፣ በሰላማዊ መንገድ ከሥልጣን ላስወግድህ ብሎ ኃይሉን ለመጠቀም ቢሻ ተቀባይነት ለማግኘቱ የሚያረጋግጥ አስተማማኝ ዋስትና ባለመኖሩ፣ ሕገ ወያኔ ባለመሻሩና የምርጫው ሕግ (አንዳንድ አወያይቻለሁ ለማለት ያህል ሰብስቦ ያነጋገረበት ሁኔታ ቢኖርም) በአገዛዙ ብቻ ተረቅቆና ጸድቆ የቀረበ በመሆኑ ነው። እስከዛሬ በአገራችን የፖለቲካ ሥርዓት ዘልቀው የመጡትን አይቷልና! ጥርጣሬን፣ አለመተማመንን፣ ሁከትን፣ አለመረጋጋትን የሚያባብስና የሚያስቀጥል እንጂ የሚያቆም አለመሆኑን ለማየት በቂና በእውቀት ላይ የተመሰረተ መረጃና ልምድም ያለው ሕዝብ በመሆኑም ጭምር ነው። ይህ በታሪካችን እንዲያ ለመሆኑ መፅሐፍ ገላጭነትን የሚጠይቅ ክስተት አይደለም። በመሆኑም ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ ይህ ከቶ የተደበቀ ጉዳይ እንደማይሆን እኛም ጥርጥር የለንም። ያም ተባለ ይህ፣ የዛሬው ልሳናችን ዋናው ትኩረቱ የዚህ የምርጫ ቧልት ላይ እንዲያተኩር ባለመሆኑ የዚህን ያክል ከማለት በላይ በእርቀት የምንሄድበት አይሆንም።

ከራሳችን አገርና ከሌሎችም አምባገነንነት ሥር ከሚማቅቁ የዓለም አገራት ታሪክ የተማርነው ጭቆናን፣ እስራትን፣ ግድያን፣ ማሳደድንና ክህደትን ሁሉ የሚፈፅመውና ሰላምን የሚነሳው መንግሥት የተባለው ተቋም ነው። ይህ መሰመር ይኖርበታል። ሕዝብ ለዘመናት ለእንዲህ ዓይነቱ ተቋም ሰለባ ከመሆን ያረፈበት ወቅት አልነበረም ቢባል ማጋነን አይሆንም ብለን እናስባለን። በእንዲህ አይነቶቹ የመንግሥት ተቋማትና በሕዝቦቹ መካከል እምነት የሚባል ነገር ሰፍኖ አያውቅም። ይባስ ብሎ አሁን ላይ በአገራችን ውስጥ በሕዝብና በአገዛዙ መካከል ብቻ ሳይሆን፣ አገዛዙ በሩን ወለል አድርጎ በከፈተላቸው ኅጠኞች፣ ፅንፈኛ ብሄረተኞችና አትዮጵያን እዚህ መቀመቅ ከከተተ በኋላ በአሳዳሪዎቹ ደጋፍ በሕዝባዊ አመጽ ከመገርሰስ የተረፈው የወያኔ ቡድን በሚያደርሱት ብጥብጥና ሁከት እንዲሁም በሚነዙት መርዘኛ ፕሮፓጋንዳ የተነሳ በሕዝብና በሕዝብ መካከል ያለው መተማመን እንዲሟጠጥ እየተሠራ ነው። ወትሮም ኢትዮጵያዊነትና ጎሳ ተኮር ፖለቲካ አብረው ተጣጥመው የሚጓዙ ሳይሆኑ፣ እንደ እሳትና ጭድ ነው ግንኙነታቸው። ምን ማለታችን እንደሆን በማያወላዳ መንገድ ለማስቀመጥ፣ ጭዱ ኅጠኝነት እሳቱ ደግሞ ኢትዮጵያዊነት ለመሆኑ የጅምላ ማንነት ወይም ሞት ከሚሉት ጉዶች በቀር ለተቀረው ሕዝብ ለቀባሪው አረዱት ዓይነት ነው የሚሆነው። እዚህ ላይ ሳንጠቅሰው ማለፍ የማይገባን ሐቅ፣ ዛሬ ላይ ኢትዮጵያ የምትገኝበት ሁኔታ ለረጅም ጊዜ ሊያውኳት፣ ሊበጠብጧት፣ ሰላም ሊነሷትና ሊያዳክሟት ለሚፈልጉ ለውስጥና ለውጭ ኃይላት የተመቻቸች አገር ሆና መገኘቷ ነው።

በተከታታይ ሁለት ሥርዓቶችን ያስወገደና ሦስተኛውን የወያኔ ሥርዓት መቃብሩ አፋፍ ላይ ያደረሰ ሕዝብ፥ የሚስማማውን መንግሥት በጋራ ለመመሥረት ገና አልተሳካለትም። በሥልጣን ላይ የሚሰየሙት አገር ማፍረስ እንጅ ሕዝብን አስተባብሮ መምራት አልተቻላቸውም። በፍርሻው ላይ በሚፈጠረው ግርግር አጋጣሚውን ተጠቅመው፥ የመንግሥት ሥልጣን ለሚነጥቁ አምባገነኖች፥ ሀገሪቷና ኑዋሪዎቿ ሰለባዎች ሆነው ዘልቀዋል። ለዚህ ሁሉ ችግር እንደ ዓይነተኛ ምክንያት ሆኖ የሚጠቀሰው፥ የአገርን ዘላቂ ጥቅም ከግል የፖለቲካ ጥቅም በላይ አሻግሮ ያለማየት ችግር ሆኗል። ሜዳው ሁሉ የተፕለቀለቀው፥ ለጊዚያዊ ሥልጣን ማርኪያ በሚሽቀዳደሙ እንጂ እምብዛም ለሀገርና ለሕዝብ ዘላቂ ጥቅም በሚጨነቁ ኃይላት እንዳልሆነ ከማንም የተሰወረ አይደለም። በወቅቱ የፖለቲካ ሹሞች የፖለቲካ ምኅዳር ሥልጣን እናገኝ ይሆናል ብለው የተኮለኮሉት ሁሉ፥ ሰሞኑን በተፈጠረው ሁኔታ፥ እንደተተኮሰባት ድኩላ ግራ ተጋብተው ደንዝዘዋል። ቆይተውም "ያመኑት ፈረስ ጣለ በደንደስ" እንዲሉ ሆኖባቸው የታሪኩን ጠባሳ እንደተሸከሙ እስከኖሩ ድረስ ይኖራሉ። እግዚኦ ለሁሉም ዓይነት አድር ባዮች! ለሰለጠነ ፓለቲካ አፈቀላጤዎች! አዲዮስ!!

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)፥ የአምባገነኖች አገዛዝ ተወግዶ በምትኩ የሕዝብ የሥልጣን ምንጭነትና ሕዝብ በዕኩልነት በአንድነት የሚኖርባት፤ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እውን እንድትሆን፥ ትግሉ የጠየቀውን መስዋዕትነት ሁሉ ከፍሎ፤ ከሕዝብ ጋር ወግኖ ለሕዝብ ጥቅም ቆሞ በየጊዜው ከተፈራረቁት አምባገነኖች ጋር ጉሮሮ ለጉሮሮ ሲተናነቅ ቆይቷል። ዛሬም በፅናት በዚሁ እንደቀጠለ አለ። በሁለተኛው የድርጅቱ ጉባኤው ላይ ባገኘው ተመክሮ ላይ በመመርኮዝ ለመደብለ ፓርቲ ፖለቲካ እታገላለሁ ካለ ወዲህ እስካሁን ድረስ ይህንኑ በኢትዮጵያ እውን ለማድረግ እየታገለ ይገኛል። ዴሞክራሲያዊት አትዮጵያም እውን እስከምትሆን ድረስ መታገሉንና ማታገሉን በአገር ውስጥም በውጭም በስፋት ቀጥሎ ይገኛል።

ኢሕአፓ በአገዛዙ ውስጥ የለውጥ ደጋፊዎች ነን በሚሉ አፈ ጮሌዎችና፥ ሥርዓቱን ለማዳን በተንቀሳቀሱ የውጭ ኃይላት አማካይነት የተደናቀፈው ሕዝባዊ የሥርዓት ለውጥ ፍለጋ አመፅ፥ የተቀናጀና በፅኑ የተደራጀ አመራር የተመራ ባለመሆኑ የተነሳ ፥ ለነዚህ ኃይላት ተንኮልና ሴራ በቀላሉ ሰለባ ለመሆን መብቃቱን በተጨባጭ በመረዳት፥ ሊከተል የሚችለውን አደጋ፥ ባፈጮሌዎች ዲስኩር ተማልሎ ተቻኩሎ ስሜታዊነትን በተላበሰ መንገድ ድጋፉን ሰማይ ጥግ ላደረሰው ሁሉ በጊዜው ጠቁሞ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው። በዚህም የተነሳ ለሃገራችን ህልውናና ለሕዝብ ካለን ክብርና ፍቅር የተነሳ ያደረግነውን እልህ አስጨራሽ ትግልና የከፈልነውን መስዋዕትነትና አኩሪ የጀግንነት ታሪካችንን፥ እንደዋዛ አጋጣሚውን በመጠቀም ጊዜ ወደ አደላበት፥ ያዘነበሉ ኃይላት ሁሉ፥ ሊያከቾለችሉት ሞክረው እንደነበር ያስተዋልነው ነው። ይሁንና ያን ሁሉ ጫጫታ በተገቢው መንገድ ስናጋልጠው ቆይተናል። ያም ሆኖ ዘመቻው ዛሬም ድረስ ያላቋረጠ ቢሆንም አሁን ላይ በአገሪቱ የተከሰተው እውነታ ቀደም ብለን በጥንቆላ ሳይሆን በመሬት ላይ ያሉትን ሁኔታዎች፤ ያሳለፍነውን ተመክሮንም በማገናዘብ በጥልቀት በመዳሰስ ትክክለኛ መረጃዎችንና እውቀትን ተንተርሰን የደረስንበትና ያሳወቅነው ድምዳሜ ነበርና የጠበቅነው ሆኗል ከማለት ውጪ የምንለው የለም።

ኢትዮጵያ ዛሬ የደረሰችበት መስቀለኛ ጎዳና እጅጉን አሳሳቢ ለመሆኑ፥ ግርግሩን ተጠቅመው በአቋራጭ ሥልጣን ለመቀራመት ካሰፈሰፉት ኃይላት በቀር ለተቀረነው ግልፅ ነው። የአገሪቱን ህልውና ለማናጋት፥ ብጥብጥና ትርምስን ሊያስከትሉ የሚችሉ እንቅስቃሴዎች ሆነ ተብለው በየቦታው በነጋ በጠባው የሚተገበሩ መኖራቸውንም ማስተዋል ከጀመርን ሰንብተናል። የነዚህን እንቅስቃሴዎች ምንነት፥ የተለሙትን እቅድና በዋናነት ማን ከጀርባቸው እንደሚዘውራቸው ሳናሰልስ ስናጋልጥና ስንታገላቸውም ቆይተናል። አሁን አገራችን ለገባችበት ቀውስና እያንዣበበ ላለው አፍራሽ አደጋ ዋናው ምክንያት የሆነውን፥

በሕዝብ የተጠላ ሥርዓት አቆነጃጅቶ ዳግም ለማስቀጥል እተሞከረ ያለው ተውኔት መሆኑን በተደጋጋሚ ገልጸናል። ይህን ማለታችንም ሕዝብን ያገለለ በመሆኑ እንጂ በሌላ አይደለም። በተጨባጭም በዚህ ምክንያት እነሆ ዛሬ ላይ በአገሪቱ ሰላምና መረጋጋት የጠፋበት፥ ሕዝብ በገዛ አገሩ በገፍ እንዲፈናቀል የሆነበት፥ ሕግን ማስከበር ተግባሩ የሆነው መንግሥት ተብየው ሃላፊነቱን ሆን ብሎ የዘነጋ በሆነበትና ሐቁ ሲነገርም የወንጀለኞችና ዘረኞች ዋና ተባባሪ ሆኖ በተገኘበት፥ ሥርዓት አልበኝነት ነግሦ አገርን ማምስ መቻሉ፥ የኑሮ ውድነትም የሕዝቡን ኑሮ ክፉኛ እያጎሳቆለ መቀጠሉ እየባሰ እንጂ ጋብ ባላለ ሁኔታ ውስጥ መሆኑ ቅልጥጥ ብሎ ወጥቷል፤ ቀጥሏልም። ብቅ ጥልቅ እያለ፤ ምርጫ ምርጫ የሚባል ነገር ሕዝባችን ያዳምጣል፤ ደግሞ ምን ሊብል ነው እያለ ይታዘባል። ባጭሩ ግን ሁኔታ ይህ ሁኖ፤ ጋሪውን ከፈረሱ ላስቀደመ ምርጫ ቧልት፥ ሕዝብ ቀደም ብለው በእንዲህ ዓይነቱ አገዛዝ ሥር በየጊዜው ተደጋግመው ይደረጉ ከነበሩ የምርጫ ቧልቶች ልምድ ላይ ተመርኩዞ፥ ልብን ፈካ የሚያደርግ ውጤት ይሰርፃል ብሎ ተስፋ ባያደርግ የሚገርመን አይሆንም ባዮች ነን።

ኢሕአፓ ይህን ሁኔታ በተመለከተ ደግሞ ደጋግሞ ብዙ ብሎበታል። በህወሓት ፊታውራሪነት ለሃያ ሰባት ዓመታት በግድ በህዝብ ጫንቃ ላይ ተጭኖ የቆየው አምባገነን አገዛዝ፥ በአገርና በህዝብ ላይ ላደረሰው ተቆጥሮ ለማያልቅ ግፍና በደል ተጠያቂ መሆኑን ራሱም ጭምር አምኖ ባለበት፥ ራሴን አድሼ፥ ለኢትዮጵያ ስርየትና መድህን ለማምጣት እኔው ሃላፊነቱን አዴፓ (ኦፒዲኦ) በተባለው ጭምብል ፊታውራሪነት ወስጃለሁ ካለበት ወቅት ጀምሮ፥ በአገሪቱ ላይ እየሆኑ ያሉትን ፖለቲካዊ፥ ኢኮኖሚያውና ማህበራዊ ቀውሶችን ሁሉ፥ በቅንነት የሚከታተል የትኛውም ዜጋ ይስታቸዋል የሚል እምነት የለንም። ይህ አሁን በሹሙ እየተመራ ያለው አገዛዝ፥ ቀውሶቹ ሁሉ ያስከተሉትን ወሳኝ ተቋማት ይዘታቸውን ሳይሆን ቅርፃቸውን ለዋውጦ ለማስቀጠል እየሰራ ያለ በመሆኑ፥ እነሆ በነበሩትና በቀጠሉት ችግሮች ላይ ሌሎች እየተጨመሩ መሄዳቸው አልቀረም። ሥርዓቱ በዚህ እስከቀጠለ ድረስ ፍዳችንና ስቃያችን እንዲሁ የሚቀጥሉ መሆናቸው አይቀሬ ነው። እንዲያ ለመሆኑ መናገራችን ትንግርት ሳይሆን ከአምባገነን አገዛዝ ባህርይ የግድ የሚመነጩ በመሆናቸው ስለሆነ የኛው አገር ታሪክ በራሱ ስለሚናገር ሌላ እማኝ ፍለጋ ከመዳከር ተቆጥበናል። ያም በመሆኑ፥ አሁን ላይ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊት አገር እንድትሆንና  አገርን እንደ አገር ለማቆየት  የሚደረገው ትግል ከባድ ፈተና ገጥሞታል ቢባል ከእውነት የራቀ አይደለም።

ምንም እንኳን ዛሬ አገራችን ውስጥ ያለው ውስብስብ፥ ምስቅልቅል፥ ሰላም የሚነሳና እስቸጋሪ ሁኔታ መሆኑ ባይዘነጋም፥ የዚህ ሁሉ ሰለባ የሆነውና ጥቃቱ ሁሉ እያመሰው የሚገኘው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከስሜታዊነት ራሱን አርቆ፥  እሩቅ አሳቢ ቅርብ አዳሪ ሳይሆን፥ አጓጉል ከሚናፈሱትና ደርዝ የሌላቸው አደናጋሪ  ቱልቱላዎችን ከቁብ ሳይቆጥር፤ ቆራጥነትን፥ ብልሃትንና ፅናትን የተላበሰ ባህርዩን እንደገና አድሶ ከፊቱ ላይ ያሉትን እጅግ ከፍተኛ መስዋዕት ከፍሎባቸው ገና ተግባራዊ ያላደረጋቸውን ግቦቹን እውን ሊያደርግ የሚችለው፥ አሁንም በሌላ ሳይሆን ራሱን በተገቢው መንገድ አደራጅቶ ትግሉን ፈር አሲዞና አጠንክሮ ከቀጠለ ብቻ ነው እንላለን።

ኢሕአፓ ቀደም ብሎ ሀገሪቱ ከገባችበት ቀውስ ልትወጣ የምትችለው  ሁሉን ባሳተፈ የሽግግር ሂደት መሆኑን በተዳጋጋሚ አስገንዝቧል። ሂደቱ ለምን? በማን? እንደሚከናወን ሀሳብ ያቀረበ ሲሆን ሽግግሩ አስተማማኝና ዘላቂነት ያለው ውጤት እንዲኖረው የሕዝብን ይሁንታ አግኝተው በሂደቱ የሚሳተፉ ኃይላት ያለምንም ተፅእኖ መክረው ዘክረው ተከራክረውና ተደራድረው በስምምነት ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው የሚያደርጉ እንደሚሆንም ያለውን ግንዛቤ የገለፀበት ነው። ይህን ሂደት እኔ አሻግራችኋለሁ ያለው ሹሙና በግርግር ሥልጣን ለማግኘት የቋመጡ፥ ለወንበር የናፈቁ፥ ጎጠኞች፥ ፅንፈኛ ብሔረተኞችና ሁሉም አይነት አድር ባዮች እየተቃወሙት አሉ። እነኚህ ሁሉ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጥቅምና ከአገር ደህንነት ጋር ተፃረው ያሉ

ኃይላት በመሆናቸው ጉዳዩን ማጣጣላቸው የሚጠበቅ ነው። ኢሕአፓ አሁንም በድጋሚ ይህ ሁሉን ያሳተፈ የሽግግር ሂደት መካሄዱ ወሳኝ ነው ብሎ ለተግባራዊነቱ አጥብቆ መታገሉን ቀጥሎበታል። ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሀገራዊ አንድነትና ኢትዮጵያን እንደ አገር የማስቀጠልና የመረከብ ትልቁ ድርሻው የሆነው ኢትዮጵያዊው ወጣት ከየቦታው ተጠራርቶ ለጋ ህይወቱን ትኩስ ጉልበቱን አስተባብሮ፤ ይህ ሂደት በኢትዮጵያ እውን እንዲሆን በማድረጉ ላይ እንዲያውለው በድጋሚ ጥሪውን እነሆ ይድረስህ ይላል!! በአቤቱታና መንግሥት ተብዬው እንዲህ ቢያደርግ እንዲያ ቢያደርግ በሚሉ አጓጉል ንትርክ ውስጥ መራኮቱም እዚህ ላይ ማብቃት ይኖርበታል ባይ ነን።

በትግላችን የሽግግር ሂደትን እውን እናድርግ!

የተሳካው ሁሉን ያሳተፈ የሽግግር ሂደት ለህዝብ ነፃ ምርጫ ጎዳና ጠራጊ ነው!!

ኢትዮጵያ ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኖራለች!!